## የ DFID መመሪያ ማስታወሻ ለድርጅቱ  ሰራተኞች እና ለፈፃሚ አጋሮች

## በኮቪድ-19 ወረርሺኝ ወቅት በሁሉም የDFID መርኀ ግብሮች ተፈጻሚ የሚደረግ ወሲባዊ ብዝበዛ፣ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳን የመከላከል የደህንነት አጠባበቅ

**ከዚህ በፊት በተከሰቱ ወረርሺኞች የደኅንነት ጥበቃ ስጋቶች ጨምረው ነበር፡፡** አዋቂ ሴቶች እና ሴት ህጻናት የተለያየ ገጽታ ላላቸው ጾታን-መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች ይበልጥ ተጋላጭ መሆናቸው የተረጋገጠ ነው፤ ከነዚህም ውስጥ በጣም የተለመዱት ቅርብ ከሆኑ ሰዎች የሚሰነዘሩ ወሲባዊ ብዝበዛዎች፣ ጥቃቶች፣ እና ወሲባዊ ትንኮሳዎች ናቸው፡፡[1] በኢቦላ ወረርሽኝ ወቅት የነበረው የአዳዲስ ምላሽ ሰጭዎች ጋጋታ ባልታሰበ ሁኔታ የወሲባዊ ብዝበዛ፣ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ እንዲፈጠር ሁኔታዎችን አመቻችቶ ሊሆን እንደሚችል ግልጽ ሆኖአል፡፡[1] የኮቪድ-19 ወረርሺኝ  ዓለም አቀፋዊና  እና መጠኑም  በዓለም አቀፍ ደረጃ ታይቶ የማይታወቅ ነው፡፡ ስለሆነም፣ ወሲባዊ ብዝበዛ፣ጥቃት እና ትንኮሳን ለመከላከል የሚደረጉ የደኅንነት ጥበቃ   ጥረቶች  እንደ  ሕይወት አድን እንጂ፣ እንደ ትርፍ ሥራ መታየት የለባቸውም፤ ይህም በተጠናከሩ የተጠያቂነት ስልቶች እና ወሲባዊ ብዝበዛ፣ጥቃት እና ትንኮሳን ለመከላከል በሚደረግ  ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ መንጸባረቅ ይኖርበታል፡፡ **የምላሽ አሰጣጡ አካል በመሆን እንደ ጤና ፣ ሰብአዊ ምላሾች ፣ ማህበራዊ ጥበቃ ፣ ትምህርት እና የመሰረተ ልማት ዘርፎች በተለይ ለወሲባዊ ብዝበዛ**፣ጥቃት እና  ትንኮሳ አደጋ ተጋላጭነት ጠንቃቃ መሆን እንዲሁም የተቀናጀ ምላሽ አሰጣጥ ማዕከል መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው ፡፡ DFID ዓለም አቀፋዊ [1]የወሲባዊ ብዝበዛ ፣ጥቃት እና ትንኮሳ መስፈርቶችን መተግበሩን መቀጠል ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም በCOVID 19 ወረርሽኝ ወቅት **ለሚኖር ወሲባዊ ብዝበዛ፣** ጥቃት እና  ትንኮሳን በቸልተኝነት ለማየት አዝማሚያ  ምንም አይነት  መለሳለስ ያለማሳየት አቋዋሙን መተግበር ይኖርበታል፡፡

**ለወሲባዊ ብዝበዛ ፣ጥቃት እና ትንኮሳ ማነው ይበልጥ ተጋላጭ የሆነው ለሚለው ማስረጃው ውስን ቢሆንም እስካሁን ያለው መረጃ ጾታ-ተኮር  ችግር እንደሆነ፣ እንዲሁም  ሴቶች እና ልጃገረዶች ይበልጥ ተጋላጭ እንደሆኑ  ያመላክታል ፡፡  ሌሎች ቡድኖችም ማለትም አካል ጉዳተኞችን፣  የወሲብ እና የጾታ ልዩነት ያላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች  እና ወንድ ህጻናትም ከፍ ያለ ተጋላጭነት እንዳላቸው በጥናት ያልተደገፈ ቢሆንም ማስረጃዎች ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል ፡፡** ስለሆነም ወሲባዊ ብዝበዛ ፣ጥቃት እና ትንኮሳን ለመከላከል የሚዘጋጁ ስትራቴጂዎች  በጠንካራ ጾታ እና በማህበራዊ አካታች ትንተና ላይ መሰረት ያደረጉ መሆናቸውን ማረጋገጥ  በጣም ወሳኝ ነው ፡፡ ይህም የDFID (አለም አቀፍ የልማት ትብብር መምሪያ)  ሰራተኞች እና አጋሮች በኮቪድ-19 ወረርሺኝ ጊዜ እነማን ለወሲባዊ ብዝበዛ ፣ጥቃት እና ትንኮሳ ይበልጥ ተጋላጭ እንደሆኑ ፣ ለምን እና እንዴት ተጋላጭ እንደሆኑ እንዲሁም ስለሚወሰዱ የመከላከል እርምጃዎች እና ስለወሲባዊ ብዝበዛ ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ ምላሽ አሰጣጥ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያስችላል፡፡ **የመርሃ ግብር ሰራተኞች ለወሲባዊ ብዝበዛ ፣ጥቃት እና ትንኮሳ  ይበልጥ ተጋላጭ የሚያደርጓቸው** ተደራራቢ ኢ-ፍትህዊነቶች ሊደርስባቸው ለሚችሉ ግለሰቦች ለምሳሌ በስደተኛ ጣብያ የሚኖሩ  ራሳቸውን እንደሴት የሚገልጹ ወንዶች (transsexual) እና የአካል ጉዳት ላለባቸው የተለያየ ዜግነት ያላቸው  ሰራተኞች የተለየ  ትኩረት መስጠታቸው ጠቃሚ ነው።

### በኮቪድ-19 ወረርሺኝ ጊዜ  ለወሲባዊ ብዝበዛ ፣ጥቃት እና ትንኮሳ   እጅግ በጣም ተጋላጭ ከሆኑት ውስጥ፡-

- የወንዶች ሠራተኞች በብዛት በሚፈልሱባቸው ማኅበረሰቦች፣  ከፍ ያለ የወሲብ ፍላጎት መጠን ጋር ተዳምሮ  **ሴቶች** ከፍተኛ ለሆነ ለወሲባዊ ብዝበዛ ፣ጥቃት እና ትንኮሳ ተጋላጭ ይሆናሉ፡፡ ለምሳሌ በኢቦላ ወረርሺኝ ወቅት በምእራብ አፍሪካ ወንድ ሰራተኞች ያለውን ሚዛናዊ ያልሆነ የስልጣን ልዩነቶችን እና ለቁሳቁሶች ያለውን ከፍተኛ ፍላጎት በመጠቀም ሴቶች  እና ህጻናት ሴቶች የእርዳታ አገልግሎቶችን ለማግኘት ሲመጡ በልዋጩ የግብረ ሥጋ ግንኙነት   እንዲፈጽሙ ያስገድዱ  እንደነበር ሪፖርቶች ወጥተዋል፡፡[1] ቤተሰብ የሚያስተዳድሩ እና በድህነት ያሉ ሴቶች ከድህነት የመቋቋም ስልቶቻቸውና አማራጮቻቸው አስገዳጅ ቤት ውስጥ የመቆየት ህጎች ተግባራዊ በሚደረጉበት ወቅት ከፉኛ ተፅእኖ ውስጥ ስለሚወድቅ ወሲብን እንደ ልዋጭ ወደማቅረብና ሌሎች አሉታዊ ስልቶች  ውስጥ እንዲገቡ ይገደዳሉ፡፡[2] ምንም እንኳን የአስገዳጅ ቤት ውስጥ መቆየት ህግ ተግባራዊ ቢሆንም ከቦታ ቦታ እንዲንቀሳቀሱ የሚገደዱ ሴቶችም የቤት ውስጥ መቆየት ህጉን በሚያስጠብቁ የፀጥታ ሀይሎች ለወሲባዊ ብዝበዛ ፣ጥቃት እና ትንኮሳ ተጋላጭ የመሆን እድላቸው ከፍተኛ ነው ፡፡[3]

---

[1] IASC (2020) Interim Technical Note: Protection from Sexual Exploitation and Abuse (PSEA) during COVID-19 Response - Version 1.0, https://interagencystandingcommittee.org/other/interim-technical-note-protection-sexual-exploitation-and-abuse-psea-during-covid-19-response

[2] IASC (2020) Interim Technical Note: Protection from Sexual Exploitation and Abuse (PSEA) during COVID-19 Response - Version 1.0, https://interagencystandingcommittee.org/other/interim-technical-note-protection-sexual-exploitation-and-abuse-psea-during-covid-19-response

[3] Fraser, E. (2020) Impact of COVID-19 Pandemic on Violence against Women and Girls, VAWG Helpdesk Research Report No. 284 ያንብቡ/ያጣቅሱ። London, UK: VAWG Helpdesk http://www.sddirect.org.uk/media/1881/vawg-helpdesk-284-covid-19-and-vawg.pdf

- ***ልጃ ገረዶች በተለይም ለአቅመ ሔዋን-የደረሱ ልጃ ገረዶች፣*** በእድሜአቸው እና በጾታቸው ምክንያት ከፍ ያለ የወሲባዊ ብዝበዛ ፣ጥቃት እና ትንኮሳ ተጋላጭነት አላቸው፡፡ የትምህርት ቤት መዘጋት እና በኮቪድ-19 ምክንያት የመጣው የኢኮኖሚ ጫና፣ ለአቅመ-ሔዋን የደረሱ ***ልጃ ገረዶች***ን ሌሎች አለአግባብ እንዲጠቀሙባቸው እና አስፈላጊ ቁሳቁሶችን ለማግኘት ሲሉ ለወሲባዊ ብዝበዛ የመጋለጣቸውን እድል ከፍ ያደርገዋል፡፡ የ***ልጃ ገረዶች*** መደበኛ የደኅንነት መረቦች/ ችግርን የመቋቋም/(safety nets )እና የሪፖርት ማድረጊያ ስልቶች ተደራሽነት እንዲሁ እክል ሊገጥማቸው ይችላል ፡፡[4] በጎዳናዎች ላይ የሚኖሩ እና የሚሰሩ ልጃገረዶች፣ አካል ጉዳተኛ እና ስደተኛ ***ልጃ ገረዶች*** በተለየ ሁኔታ ለወሲባዊ ብዝበዛ፣ጥቃት እና ትንኮሳ ተጋላጭ ናቸው፡፡
- ***ህጻናት ወንድ ልጆች*** በእድሜአቸው ምክንያት በተለየ ሁኔታ ለወሲባዊ ብዝበዛ፣ጥቃት እና ትንኮሳ ተጋላጭ ናቸው። ወንድ ህጻናት ልጆች ከተንከባካቢዎቻቸው በመለየታቸው(ይሄውም ተንከባካቢዎቻቸው መቆያ ውስጥ በመግባታቸው ወይም በጸና ህመም/ሞት) ምክንያት ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ ሊደርስባቸው ይችላል፡፡ ትምህርት ቤቶች መዘጋታቸው በደህንነት መረቦች ተደራሽነት ላይ ተጽእኖ ይፈጥራል፣ በተለይም ከፍ ያለ ተጋላጭነት ላላቸው ቤተሰብ የሚመሩ ፣ ከወላጅ ወይም ጠባቂ የተለዩ ፣ ግጭት/ጦርነት ተጽእኖ ያሳደረባቸው ወይም በስደተኛ ጣብያዎች የሚኖሩ እና/ወይም የጎዳና ተዳዳሪ ለሆኑ ወንድ ህጻናት ልጆችን ላይ በሚኖረው ተደራሽነት ላይ ተጽእኖ ይፈጥራል፡፡
- ከአካል ጉዳት ጋር የሚኖሩ ሰዎች በተለይም ሴቶች እና የአእምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው ግለሰቦች በሚደርስባቸው ከፍተኛ መድልኦ ምክንያት ከፍ ላለ የወሲባዊ ብዝበዛ፣ጥቃት እና ትንኮሳ ተጋላጭነት አላቸው፡፡ በተንሰራፋው ጎጂ ባህል መሰረት ከአካል ጉዳት ጋር የሚኖሩ ግለሰቦች ከክፉያ ስራዎች ስለሚገለሉ ለኑሮ የሚያስፈልጋቸውን ለማግኘት ወሲብን እንደ ልዋጭ የማቅረብ አማራጭን ይይዛሉ፡፡ ከአካል ጉዳት ጋር የሚኖሩ ግለሰቦች የአካል ጉዳት ከሌላቸው ግለሰቦች ጋር ሲነጻጸሩ ረዘም ላለ ጊዜ የወሲባዊ ብዝበዛ፣ጥቀት እና ትንኮሳ ሊደርስባቸው ይችላል ፡፡ ይህም የሆነው ወሲባዊ ብዝበዛ፣ጥቃት እና ትንኮሳን ሪፖርት ማድረግን በሚመለከት በሚደረጉ የግንዛቤ ማስጨበጫ እንቅስቃሴዎች ስለማይካተቱ እና የወሲባዊ ብዝበዛ፣ጥቃት እና ትንኮሳ ሲከሰት ለማጋለጥ ቢሞክሩ እንኳን የመታመን እድላቸው ዝቅተኛ ስለሚሆን ነው፡፡[5]
- ***ተመሳሳይ ፆታ ጋር የፍቅር እና የወሲብ ፍላጎት እና መሰል ሁኔታ ያላቸው ግለሰቦች (LGBTQ+)፣*** መጠነ ሰፊ በሆነው የምጣኔ ሀብታዊ፣ ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ መገለል ምክንያት ከፍተኛ የሆነ የወሲባዊ ብዝበዛ፣ጥቃት እና ትንኮሳ ተጋላጭነት አላቸው፡፡ ከተመሳሳይ ጾታ ጋር የፍቅር እና የወሲብ ግንኙነት እና መሰል ሁኔታ ያላቸው(LGBTQ+) የእርዳታ ሰራተኞችም ለወሲባዊ ብዝበዛ፣ጥቃት እና ትንኮሳ ከፍተኛ ተጋላጭነት አላቸው፡፡[6]
- ***በወቅታዊ እና በመከሰት ሂደት ላይ ባሉ ቀውሶች ውስጥ ያሉ በተለይም በስደተኛ መጠለያ ጣብያዎች ወይም ጥቃትን ሸሽተው የሚገኙ ሰዎች*** በተለየ ለወሲባዊ ብዝበዛ፣ጥቃት እና ትንኮሳ ከፍተኛ ተጋላጭነት አላቸው፡፡ ይህም በእርዳታ ሰራተኞች ላይ ያላቸው ጥገኝነት ከፍተኛ በመሆኑ እና ስለ ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ መረጃ የማግኘት እድላቸው ውስን የመሆኑ ውጤት ነው፡፡[7]
- ***በግንባር ቀደም አገልግሎት ሰጪ ሆነው የሚሰሩ ሴቶች (ለምሳሌ የጤና ምላሽ አካል)*** በስራ ባልደረቦች፣ በታካሚዎች እና በታካሚ ቤተሰቦች የሚፈጸሙ የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳን ጨምሮ ከፍ ላለ የስራ ቦታ ላይ ጥቃት ተጋላጭ ናቸው፡፡ ይህም በኮቪድ-19 ምክንያት በሚመጣው ከፍተኛ ጭንቀት፣ በጤናው ስርዓት ውስጥ ባለው የስልጣን ማስባሰብ የተነሳ እና እና የግል መከላከያ ቁሳቁሶች (PPE) እጥረት ይበልጥ ይባባሳል፡[8]

## ከወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት፣ እና ወሲባዊ ትንኮሳ ደኅንነት ጥበቃ፡- በኮቪድ-19 ወረርሺኝ ጊዜ መከላከልን እና ምላሽ አሰጣጥን ማረጋገጥ

ምንም እንኳን **ኮቪድ-19 አዳዲስ የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ ግዴታዎችን ይዞ ባይመጣም አሁን ባለው ሁኔታ ሁሉም የመርሃ ግብር ሰራተኞች በመርሃ ግብሮቻቸው ከፍ ያለ የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ ተጋላጭነት ስላለ ልዩ ትኩረት መስጠት አለባቸው፡፡** የDFID (ዓለም አቀፍ የልማት ትብብር መምሪያ) የመርሃ ግብር ሰራተኞች በመርሃ ግብሮቻቸው ለተከሰቱ የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳዎች መፍትሔ ለመስጠት የመመሪያውን መደበኛ ሂደቶች እንዲከተሉ ይጠብቃል፡፡ ይህም የተጠናከረ ትጋትን ፣እንደ አስፈላጊነቱ ለህጻናት የተጠናከረ አጠባበቅ ትጋትን ጨምሮ፣ የመርሃግብር ንድፍ ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳን ከግምት ውስጥ ያስገባ እና በወቅታዊ የሥርዓተ-ጾታ እና ማኅበራዊ አካታች ትንተና ላይ የተመሠረተ መሆኑን ማረጋገጥን ያካትታል፡፡ ለሰብአዊና ድንገተኛ አደጋዎች የተዘጋጁት የDFID Smart Rule 17 በአስቸኳይ የኮቪድ-19 መርሃ ግብሮች ላይ ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡ እንዲሁም መደበኛ የእድገት ውስንነት አካል ጉዳት አገልግሎት (DDA) የመጀመሪያዎቹ የገንዘብ ድጋፎች ከተለቀቁ በኋላ መጠናቀቅ እንደሚችሉም ልብ ይበሉ፡፡ ነገር ግን የመርሃ ግብሩ የበላይ ሀላፊዎች ማንኛውም

---

[4] Reference: Girls' Education Challenge (2020) Safeguarding, Protection and COVID-19 Guidance Note for Projects – 2 nd Edition, https://dfid-gec-api.s3.amazonaws.com/production/assets/34/Safeguarding_and_COVID-19_Partner_Guidance_April_2020.pdf

[5] Palladium (2019) Response to the International Development Committee's Inquiry into DFID's work on Disability, http://data.parliament.uk/writtenevidence/committeeevidence.svc/evidencedocument/international-development-committee/dfids-work-on-disability/written/96834.html; DFID (2018) Sexual Exploitation Abuse and Harassment in the International Aid Sector: Victim and Survivor Voices: Main Findings from a DFID-Led Listening Exercise, https://assets.publishing.service.gov.uk/government/uploads/system/uploads/attachment_data/file/749741/Listening-Exercise1.pdf

[6] chauerhammer, V (2018) Reporting Complaint Mechanisms, Barriers to Reporting and Support in the Aid Sector for Sexual Abuse, Exploitation and Harassment, VAWG Helpdesk Research Report No.207 London UK: VAWG Helpdesk https://assets.publishing.service.gov.uk/media/5c59799fed915d045f3778a4/VAWG_Helpdesk_Report_207_Reporting_mechanisms_SEAH.pdf

[7] International Committee of the Red Cross (ICRC) (2020) COVID-19: Inclusive Programming – Ensuring Assistance and Protection Addresses the Needs of Marginalized and At-risk People, International Committee of the Red Cross, https://reliefweb.int/report/world/covid-19-inclusive-programming-ensuring-assistance-and-protection-addresses-needs

[8] Yaker, R. (2020) Securing the Safety and Wellbeing of Women Frontline Healthcare Workers in the COVID-19 Response, GBV AoR Helpdesk, http://www.sddirect.org.uk/media/1896/202003-securing-safety-and-wellbeing-of-women-frontline-healthcare-workers-covid-19_final_version.pdf

ተጋላጭነት ከሚጠበቀው ውጤት ጋር ተመጣጣኝ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ ከ DFID (ዓለም አቀፍ የልማት ትብብር መምሪያ) መርሃግብሮች ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሁሉም የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ ሪፖርቶች ወድያውኑ በ reportingconcerns@dfid.gov.uk ኢሜል በመላክ ሪፖርት መደረግ አለባቸው፡፡

**የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳን ለመከላከል የሚደረገውን የደኅንነት ጥበቃ ለማገዝ የመርሃ ግብር ሰራተኞች የሚከተለውን ማድረግ አለባቸው፡-**

- **ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳን መከላከል እና የሚሰጠው ምላሽ ጠቃሚነት ለአጋሮች በተከታታይ በመንገር ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳን እንዴት በመላ መርሃ ግብሮቻቸው መታገል/ማስቀረት እንደሚቻል የመሪነትን ሚና ይውሰዱ ፡፡** DFID (ዓለም አቀፍ የልማት ትብብር መምሪያ) ፣አጋሮች እየጨመረ ለመጣው የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት፣ እና ወሲባዊ ትንኮሳ ተጋላጭነት መገንዘባቸውን እንዲሁም የኮቪድ-19 ማስማሚያዎች፡-የአጭር እና ረጅም ጊዜ ሰራተኞች እና ተባባሪዎች ማንነት ማጣሪያ መደረጉን፣ የሥነ-ምግባር ደንብ መፈረሙን እና የሰራተኞች ስልጠና መስጠቱን ጨምሮ፣ የደኅንነት ጥበቃ እርምጃዎች ቅድሚያ መስጠታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡ አስቸኳይ የሰራተኛ ቁጥር ከፍ የማድረግ ሂደት ውስጥ እና የአጭር ጊዜ ሰራተኞች ቅጥር ቢኖርም እንኳን ፣ወሲባዊ ብዝበዛ፣ጥቃት እና ትንኮሳን የመከላከል ስራ ሰራተኞች እና ተባባሪዎች ወደ ስራ ከመሰማራታቸው በፊት የማንነት ማጣሪያ እና ስልጠና ውስጥ መካተቱ በጣም ወሳኝ ነው፡፡
- **የሚቻል ከሆነ አጋሮች በሃገር ውስጥ ካሉ እንደ ወሲባዊ ብዝበዛን እና ጥቃትን መከላከል የትብብር መረቦች (PSEA) ጋር ተጣምረው እንዲሰሩ ያግዙ ፡፡** የኤጀንሲ ወሲባዊ ብዝበዛና ጥቃት መከላከል የትስስር መረቦች (PSEA) በመደበኛነት የሚመራው በተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ ድጋፎች አስተባባሪ / ነዋሪ አስተባባሪ (UN Humanitarian Coordinator/Resident Coordinator) ሆኖ በትስስር መረቦቹ አስተባባሪ ድጋፍ ሰጪነት ነው፡፡[9] እነዚህ ተግባራዊ በማይሆኑበት ቦታ የመርሃ ግብር ሰራተኞች ከሌሎች መረቦች ጋር ለምሳሌ በህጻናት አጠባበቅ ወይም ጾታን መሰረት ባደረጉ ጥቃቶች (GBV) መከላከል ላይ ከሚሰሩ አጋሮች ጋር ጥምረት እንዲፈጥሩ ማበረታታት አለባቸው፡፡[10]
- **የመርሃ ግብሩ በጀት የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ ደኅንነት ጥበቃን ተግባራዊ ለማድረግ በቂ መሆኑን ያረጋግጡ፡፡ አዲስ መርኀ-ግብር በሚወጣበት ወቅት** በተገመገመው የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ ስጋት መጠን ላይ በመመስረት የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳን ለመከላከል የደኅንነት ጥበቃ ፕሮግራም በጀት መያዝ አለበት፡፡ ነባር መርሃግብሮች ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳን በአግባቡ መከላከል እና ምላሽ መስጠት መቻሉን ለማረጋገጥ የበጀት ክለሳ (ወቅታዊ በሆነው የሀብት ምደባ ውስጥ) ሊያስፈልጋቸው ይችላል፡፡ ይህም ለሚመጡ የቴክኒክ ባለሙያዎች የሚውል ገንዘብን ሊያካትት ይችላል፡፡
- **ከኮቪድ-19 ጋር ግንኙነት ያላቸውን የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ ስጋቶችን** ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ከመርሃግብሮች ጋር የተያያዘ ማንኛውም አዳዲስ የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ ተጋላጭነትን ይለዩ። ከፍተኛ የሆነ የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ ተጋላጭነት ስጋት በአብዛኛው የሚገኝበት ሁኔታ ስለሆነ የመርሃግብር ሰራተኛው መርሃግብሩ የቱ ጋር ትልቅ የስልጣን አለመመጣጠን እንዳለበት ማጤን አለበት ፡፡ ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳን በጤና፣ በሰብአዊ ስራ፣ ማኅበራዊ ጥበቃ፣ ትምህርት፣ መሰረተ ልማት መርሃግብሮች ውስጥ ለመለየት ልዩ ትኩረት መሰጠት አለበት። እንዲሁም የመርሃግብሩ ሰራተኞች ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ በኢንተርኔት መስመር ላይ እና ከኢንተርኔት መስመር ውጪም ሊከሰት እንደሚችል ማወቅ አለባቸው፡፡ መርሃግብሮችን ከርቀት ማስተዳደር እና ትግበራ ወቅት የመርሃግብር ሰራተኞች እየጨመረ የመጣውን በደል ማድረስን በቀላሉ የመለየት ችግር መገንዘብ፣ የጥቃት ሰለባዎች አገልግሎት እንዲያገኙ የማገዝ፣ ምርመራ የማድረግ እና ለተጎዱ ማኅበረሰቦች በቂ ተጠያቂነት መኖሩን ማረጋገጥና ስለአዳዲስ ስጋቶች ንቁ መሆን አለባቸው፡፡ የመርሃግብር ሰራተኞች ፈጠራ የታከለባቸው የግንኙነት መንገዶችን በመፈለግ አስገዳጅ በቤት ውስጥ የመቆየት እገዳ ከተጣለባቸው ማኅበረሰቦች ጋር መገናኘት ፣ ምርመራዎችን በርቀት የማካሄድ እድልን ማሰስ፣ ከሴቶች መብት ተሟጋች ቡድኖች ወይም የአካባቢው አገልግሎት ሰጪዎች ጋር መተባበርን ጨምሮ ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ ስጋቶችን ለመቋቋም የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችን ማቀድ አለባቸው ፡፡

**የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳን ሪፖርት አደራረግ እና ምላሽ አሰጣጥን ለማገዝ የመርሃግብር ሰራተኞች ማድረግ ያለባቸው፡-**

- **አጋሮች የማህበረሰቡ አባላት ስለ ደኅንነት ጥበቃ ሂደቶች የተሳለጠ መረጃ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ፣ ቅሬታ እንዴት እንደሚያቀርቡ፣ ተዛማጅ አገልግሎቶችን እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ፣ መደበኛ አሠራሮችን ለማግኘት የሚቸገሩትን ማለትም እንደ ሴቶች ፣ ሴት እና ወንድ ልጆችን እና ከአካል ጉዳት ጋር የሚኖሩ ሰዎችን ጨምሮ ከግምት ውስጥ ማስገባታቸውን ማረጋገጥ፡፡** አስገዳጅ በቤት ውስጥ ቆይታ እና የለይቶ ማቆያ እርምጃዎች የብዙ ሰዎችን የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት፣ እና ትንኮሳ መልእክቶችን እና አገልግሎቶችን የማግኘት ዕድላቸውን ሊገድቡ ይችላሉ፡፡ የመርሃግብር ሰራተኞች እርዳታ ሁልጊዜም በነፃ የሚሰጥ እንደሆነ እና አሳሳቢ ሁኔታን እንዴት ሪፖርት ማድረግ እንደሚቻል አፅንኦት በመስጠት እንደ ተንቀሳቃሽ/ በሞባይል ስልኮች እና የሬዲዮ ፕሮግራሞች የመሳሰሉ የተለያዩ የግንኙነት ዘዴዎችን እንዲጠቀሙ አጋሮችን ማገዝ አለባቸው ፡፡ መርሃግብች የማኅበረሰብ አባላት አስገዳጅ በቤት ውስጥ የመቆየት ሁኔታ ውስጥ ደህንነታቸው ተጠብቆ እንዴት ሪፖርት ማድረግ እንዳለባቸው ከግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡ በአንዳንድ ልዩ ሁኔታዎች ማለትም በከፍተኛ ደረጃ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዕውቀት በማይኖርበት ጊዜ፣ ሴቶች እና ልጃገረዶች ተንቀሳቃሽ ስልኮች በማይኖራቸው ጊዜ፣ ወይም ሪፖርት ለማቅረብ የሚያስተማምን ሁኔታ በማይኖርበት ወቅት በአካል ሪፖርት ማድረግ ተመራጭ ሊሆን ይችላል።፣ ሠራተኞች በዋናነት በርቀት የሚሰሩ ከሆነ፣ ግለሰቦች የርቀት የመገናኛ ዘዴዎችን ለመጠቀም እርግጠኛ በማይሆኑበት ጊዜ ውስጥ ህገ-ወጥነት ፣ ሥነ-ምግባር የጎደለው ፣ ወይም ትክክል ያልሆነ ነው ተብሎ በሚታሰብ ድርጊትን የሚያጋልጥ ሰርዓት በድርጅቶች ውስጥ መኖርን ከግምት ውስጥ መስገባት አለባቸው።
- **DFID (ዓለም አቀፍ የልማት ትብብር መምሪያ) በሚደግፋቸው በሁሉም መርሃግብሮች ውስጥ ለጥቃት ሰለባዎችና እና ጥሰቶችን ለሚያጋልጡ ቅድሚያ የመስጠቱ ሥራ መቀጠል አለበት።** ዓለም አቀፍ የልማት ትብብር መምሪያ አጋሮች በአገሪቷ የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ ሰለባ ግለሰቦችን ለመርዳት ከነባር አገልግሎቶች ጋር ግንኙነት እንዲፈጥሩ ማበረታታት ይኖርበታል ። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ወሲባዊ ብዝበዛ እና ጥቃትን የሚከላከል አስተባባሪ መድቦ ከሆነ ይህ አሰራር መበረታታት ይገባዋል። ጾታን መሰረት ባደረገ ጥቃት (GBV) እና የሕጻናት ጥበቃ ድጋፍ አገልግሎቶች ላይ የሚሰሩ ሰብዓዊ ድርጅቶች፣ ለኮቪድ - 19 የሰብአዊ ምላሽ ዋና አካል ተደርገው መታየት ያለባቸው ሲሆን፣ ከወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ ጥቃት ሰለባዎች

---

[9] IASC (2020) Interim Technical Note: Protection from Sexual Exploitation and Abuse (PSEA) during COVID-19 Response - Version 1.0, https://interagencystandingcommittee.org/other/interim-technical-note-protection-sexual-exploitation-and-abuse-psea-during-covid-19-response

[10] ይህም በሥራ ላይ የዋሉ ከሆነ ወይም ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት (GBV) ወይም የሕጻናት ጥበቃ ጋር የተያያዙ አግባብነት ያላቸው የቅንጅት ዘዴዎች ካሉ ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ወይም የሕጻናት ጥበቃ ንዑስ-ስብስቦችን ሊያካትት ይችላል ፡፡

እንዲሁም በተንሰራፋው ጾታ- ተኮር ጥቃት ሰለባ የሆኑ ሴቶች፤ ልጃገረዶች ና ጥቃት የሚደርስባቸው ሕጻናት ለእርዳታ የሚላኩባቸው ቦታዎች ሊሆኑ ይገባል። የሚቀርቡት አገልግሎቶች አስተማማኝ በማይሆኑበት ሁኔታ ውስጥ የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ ጥቃት ሰለባዎችን ለመርዳት የተሻለ አገልግሎት ለማቅረብ በመርሃግብራቸው ውስጥ ወይም በሀገሩ ውስጥ በሚገኘው ዋና መሥሪያ ቤታቸው ውስጥ ዕድል ይኖር እንደሆነ የመርሃግብር ሰራተኞች ማጤን ይኖርባቸዋል።

- **DFID (በዓለም አቀፍ የልማት ትብብር መምሪያ) የገንዘብ ድጋፍ ከሚደረግላቸው መርሃግብሮች ጋር የተዛመዱ ሁሉም የደኅንነት ጥበቃ ስጋቶች በ[reportingconcerns@dfid.gov.uk](mailto:reportingconcerns@dfid.gov.uk) የኢሜል ሪፖርት መደረጋቸውን እና አጋሮችም እነዚህን ሪፖርቶች በትኩረት ማየታቸውን እና እንዲሁም የጥቃት ሰለባውን ለመመዝገብ (ቃለ መጠይቅ ማድረግ)፣ ለመመርመር እና ለመርዳት ተገቢውን እርምጃ መውሰዳቸውን ያረጋግጡ ፡፡** በቤት ውስጥ የመቆየት ግዳጅ የጥቃት ሰለባዎችን ደህንነት ማረጋገጥ እና ሕይወት አድን አገልግሎቶችን እንዳያገኙ ወይም ምርመራዎችን እንዲያዘገዩ ለማድረግ እንደ ምክንያት ወይም ሰበብ ሊቀርብ አይገባም። የሚቻል ከሆነ የርቀት ምርመራ አማራጭ እንደ ጊዜያዊ መፍትሄ ከግምት ውስጥ መግባት አለበት። DFID (የዓለም አቀፍ የልማት ትብብር መምሪያ) የደህንነት አጠባበቅ ምርመራ ቡድን ምክር እና ድጋፍ ለመስጠት ዝግጁ ናቸው።

**በ ኮቪድ-19 ወቅት በዓለም አቀፍ የልማት ትብብር መምሪያ( DFID) ድጋፍ የሚደረግላቸው መርሃግብሮች በሙሉ የአጠባበቅ መመሪያ**

ዓለም አቀፍ የልማት ትብብር መምሪያ የአጠባበቅ እይታ ገጾች

የተቋማት ትስስር ቋሚ ኮሚቴ 2020 ጊዜያዊ የቴክኒካዊ ማስታወሻ፡- በኮቪድ-19 ምላሽን ወቅት ከወሲባዊ ብዝበዛ ጥቃት እና በደል ጥበቃ(PSEA) - ስሪት 1.0

የተቋማት ትስስር ቋሚ ኮሚቴ 2020 ኮቪድ -19፡-መገለል የደረሰባቸውን እና ተጋላጭ የሆኑ ሰዎችን በመገናኛ እና በማህበረሰብ ተሳትፎ ውስጥ እንዴት ማካተት እንደሚቻል

**የደህንነት አጠባበቅ ስጋቶች በሚከተሉት መንገዶች ሊቀርቡ ይችላሉ፡-**